## የድህነትና ስቃይ ጌቶች

ግርሃም ሀንኩክ የተባለ ጋዜጠኛና የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ የድህነት ጌቶች (Lords of poverty) ብሎ የጻፈው አንድ መጽሀፍ ትዝ ይለኛል። መጽሀፉ በታዳጊ ሐገሮች ያለውን ድህነትና ፈርጀ ብዙ ውልጃዎቹን ለመታደግ በሚል የተቋቋሙትን ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ሐገር በቀልና አለም አቀፍ ‘ የበጎ አድራጎት’ ድርጅቶች እኩይ ተግባር ዘርዝሮ የሚያስረዳ ነው። በዚህ መጽሀፍ በአመት ከመቶ ሺ ዶላር በላይ ከሚከፈላቸው ‘ የድህነት ኤክስፐርቶች’ ጀምሮ ድህነትን ለማሸነፍ ምንም ፋይዳ የሌላቸው ነገር ግን የምዕራቡን አለም ፋብሪካዎች ምርታማ ለማድረግና ሰራቶኞቻቸው ቅጥራቸው ይቆይ ዘንድ ተፈብርከው ከምዕራቡ አለም ወደ ድሆች ሐገራት ስለሚጋዙት የትየለሌ ቁሳቁስ ይተርካል። የአንዱ ድህነት ለሌላው የኑሮ መሰረት መሆኑ ነው እንግዲህ። ይሄን መጽሀፍ ያነበበ የእኛዎቹን ገዢዎቻችንን ተግባር እግረ መንገዱን በአርምሞ መመርመሩ አይቀርም። ለማንኛውም የሀንኩክን ርዕስ እንዋስና እስቲ ደግሞ የእኛን ሐገር ሌሎቹን አይነቶች የስቃይና የድህነት ጌቶች ጉዳይ እንመልከት።

ሐገር ቤት ሳለሁ በአንድ ወቅት የመስሪያ ቤታችን ስራ አስኪያጅ አራተኛ ክፍል ያጠናቀቀ ቄስ ነበር። እርሱም በአንድ ወቅት ‘ የህዝብ ብሶት’ ወለደውና ቅስናውን ትቶ ነፍጡን አንግቦ ሲያበቃ ‘ ታጋይ’ ሆነ። ከአመታት ተኩስ በሁዋላ እራሱን እመዲናይቱ ከተማ ባለ አንድ የመንግስት ድርጅት ውስጥ ‘ስራ አስኪያጅ’ ሆኖ አገኘው !! ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም ይላል የሐገራችን ሰው። እርሱ ደግሞ በአንጻሩ ይታገሉታል እንጂ አይታደሉትም ወይም በትምህርትና ስራ ልምድ አያገኙትም ይል ይሆናል። እናም የእኔ አለቃ እምስራቅ አውሮፓ የተማሩ ሰው ነበሩ ይህ ቄስ ታጋይ ደግሞ የአለቃዬ አለቃ መሆኑ ነው። አለቃዬ ‘ፍራቻቸው’ ታዲያ አይጣል ነው ። ታጋይ አለቃቸውን ለማስደሰት አድርጉ የተባሉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር። የበታቾቻቸው በዚህ እንበሳጭ ነበር ። አንድ ቀን ግን የአለቃዬ ፍራቻ ምክንያቱ ሁሉ ነገር ፍንትው አድርጎ የሚያሳየኝ አጋጣሚ ተከሰተ። ከስራ መውጪያ ሰዓት በኋላ በአንዱ ቀን ሻይ ቡና ለማለት አንድ ካፌ ጎራ አልንና ጨዋታን ጨዋታ ሲያመጣው የአለቃዬን የቀድሞ ጀብድና የአሁኑን ፍርሃት ሳቢያ ልረዳው ቻልኩ።

የቀድሞው አለቃዬ በዘመነ ደርግ በከፍተኛ ትምህርት ምደባ መምሪያ (ት/ት ሚኒስቴር ውስጥ ይገኝ የነበረ ተማሪዎችን እየመለመለ ወደ ምስራቅ አውሮፓ ይልክ የነበረ) በከፍተኛ ሀላፊነት ቦታ ላይ ያገለግሉ ነበር። በዘመኑ ለፓርቲው የታመኑ በአቅማቸው አለቃ ቢጤ ሳይሆኑ አልቀረም። በአንዱ በተረገመ ቀን ‘ጓድ’ ለገሰ አስፋው በሚመራው ትልቅ ስብሰባ ላይ መንግስትን የሚሸነቁጥ ሀሳብ ይሰነዝራሉ። ስብሰባው እንዳለቀ ወደ አቶ ለገሰ ቢሮ ይጠሩና ምን ለማለት ፈልገው እንደሆነ ይጠየቃሉ። ይህን ጨዋታ ሲያጫውቱኝ የለገሰ አስፋው ቢሮ ስፋት የአንድ ሜዳ እሩብ ይሆናል ብለውኛል፤ (በእርሳቸውና እርሱ በባለ ግርማ ሞገስ ወንበሮችን ማሆጋኒ ጠረጴዛ ተከቦ ባለበት ስፍራ መሀል ሰፊ ክፍተት አለ) ይጋነን ይሆናል ቢባልም እኔም በሁዋላ ላይ በአንዱ አገር አቀፍ የእርዳታ ድርጅት እንዲህ አይነት ቢሮ አጋጥሞኛል። እናም ለጓድ ለገሰ ሀሳባቸውን አስረድተው ተላማምጠው ንግግራቸው ለክፉ የታለመ እንዳልሆነ ካስረዱ በሁዋላ ‘ጓውዱ አንድ ጠበቅ ያለ ማስጠንናቀቂያ እንደነገራቸው ያስታውሳሉ። መሰንበት የምትፈልግና ልጆችህን ማሳደግ የምትመኝ ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ ብታስብበት ይሻላል !!!

ያ ማስጠንቀቂያ እርሱኑ ተከትሎ የሆነው ሁሉ የቀድሞ አለቃዬን ሕይወት እስከ ወዲያኛው የለወጠ ጉዳይ ሆኖ ቀረ። (ለለገሰ አስፋው ምንም ላይሆን ቢችልም) ከዚያን ቀን ጀምሮ የሰውየው ማምሻ መጠጥ ቤት ሆነ። ትከሻን ማመን ቀረ። የትኛውም ቦታና ሰአት ላይ እስር አልያም ግድያ ቅርብ የሆነ ሀሳብና ሁናቴ ሆነና ቀረ። ‘የሱሪዬ ጫፎች እጫማዬ ስር ብትንትናቸው እስኪወጣ ድረስ ዝልዝል ያልኩ ዕብድ ሆንኩ’ ይላሉ ሰውየው። የተባለውም አልቀረ እስርም መጣ በጉልምስና ወራትም ግርፋት ተከተለ። ከዚያ በሁዋላ የጉብዝና ወራት እንደጉም በነኑ ። ከእስር ቤት በሁዋላ አዲሱ ማንነት በስቃይ ተምጦ፤ በፍራቻ ታጅሎ ተወለደ። እኛ አለቃችንን ስናገኛቸው በሕብረተሰቡም፤ በሰው ልጅም

ሰብአዊነት ተስፋ የቆረጡ ለመኖር ብቻ የሚኖሩ አይነት ሰው ሆነው ነበር። ይህ የእኔ የቀድሞ አለቃዬ ብቻ ሳይሆን የብዙዎቻችን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ነው። እንዴት ካሉ ልብ ብለው ይከታተሉኝ።

መለስ ዜናዊ አንዳንዶች ‘ ጂኒየስ’ ነው ይሉታል። አዎ ጅንየስ የሚለው ቃል ‘ጅኒ’ ከሚለው የአረብኛ ቃል መምጣቱን ለሚያውቅ አዎ መለስ የኋለኛውን ነው ማለቱ አይቀርም። የእርሱ ጅንየስነት የኢትዮጵያውያንን ስነ ልቦና (psyche) ጠንቅቆ ማወቁ ላይ ነው ያረፈው። ኢትዮጵያዊ ማለት ለዘመናት በረሀብ የተገረፈ፤ በፍትሕ እጦት የተንገላታ እንዲያውም የሰቆቃ ሰለባ የሆነ ድሀ ሕዝብ እንደሆነ ጠንቅቆ አውቋል። የአገዛዙም መሰረት ይኸው ነው። በረሀብ ሲንገላታ የቆየ ህዝብ በቀን ሶስት ጊዜ ትበላለህ ካልከው የሕይወቱን ቋጠሮ / button / ተጫንከው ማለት አይደለምን? አባይን እንገድብና ኢትዮጵያ ማርና ወተት የሚዘንብባት አዲሲቷ እዝራኤል ትሆናለች ካልከው መንፈስ መናወዙ በህልም አለም ተንሳፎ በዘመነ  ህይወቱ ይሁን አይሁን ለማያውቀው ፕሮዤ ከደሞዙ መክፈሉ ይቀራል? ይህንኑ ህዝብ ‘ እምቢ’ ሊል ሲፈልግ ‘ልጆችህን ማሳደግ አትፈልግም?’ ስትል ካስታወስከው ሊረሳው የሚፈልገውን ስቃዩን ቆሰቆስከው ወደ ፍርሃት ጉድጓዱ መለስከው ማለት አይደለምን? ይኸው ነው የመለስና የተከታዮች ፍልስፍና ዋልታና ማገር።

የስነ ሳይኮሎጂውን ስቃይ/ሰቆቃ (psychological trauma)ዊኪፒዲያ እንዲህ ይፈታዋል። ( መምህራኑ ለምስክርነት ብዙም አይበቃም ቢሉም ይህ ጽሁፍ አካዳሚክ ስላልሆነ እንጠቀምበት ) ሰቆቃ ማለት በአዕምሮና በሰዎች የአስተሳሳብ ሂደት ላይ ስቃዩን ባደረሰው ገጠመኝ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ማለት ነው።  ይህም ወደ ድህረ ስቃይ መመሳቀል/ post- traumatic stress disorder/ የሚመራ ሲሆን ጉዳቱ በአዕምሮ ሴሎች ላይና የአዕምሮ ኬሚስትሪ ላይ ጊዚያዊ ወይም እንደ ሁኔታ ዘለቄታዊ አሉታዊ ለውጥ ያመጣል። የስነልቦናዊ አሉታዊ ውጤቱን ደግም እንዲህ ሲል ያብራራዋል ፡

> *“A traumatic event involves a single experience, or an enduring or repeating event or events, that completely overwhelm the individual's ability to cope or integrate the ideas and emotions involved with that experience. The sense of being overwhelmed can be delayed by weeks, years or even decades, as the person struggles to cope with the immediate circumstances.” « http://en.wikipedia.org/wiki/Psychological_trauma»*

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ አይነት ባሉ ሐገሮች ያሉትን ነባሪያዊ ባህላዊና ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ለሚያስገባ አንባቢ ዜጎች በሕይወታቸው ምን ያህል ተደጋጋሚ ስቃዮች እንደሚደርሱባቸው መረዳት አያዳግትም።ተደጋጋሚ ስቃይ የሚደርስበት ሰው ደግሞ በተለይም ምንም አይነት ማህበራዊ ዕገዛ በማይገኝበት ሐገር እንዲይውም ያው አጥቂው ሀይል ሆነ ብሎ ማህበረሰቡ ተጠቂውን ግለሰብ እንዲያገል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ሲያደርግ ችግሩ ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ መረዳት ሊቅ መሆንን አይሻም። ለምሳሌ በዙውን ጊዜ መንግንስት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንና ደጋፊዎቻቸው ናቸው ያላቸውን ሰዎች በመጀመሪያ ከስራ ያፈናቅላል። ከስራ መፈናቀል ማለት የአንድን ሰው ማንነት ውልቅልቁን የሚያወጣ ግለሰቡ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ነጻነት የሚገፍና የማዋረድ አላማ ያለው ተግባር ነው። በዚህም አያበቃም ግለሰቡ ይታሰራል፤ አካላዊ ስቃይም ይፈጸምበታል። ይሄ ሁሉ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚካሄድ ተግባር አይደለም የተሰበረ ማንነትንና የተዋረደ ፈሪ ማህበረሰብን የመቀፍቀፍ ውጥን እንጂ።

ኢፍትሀዊነትን እንታገላለን ያሉ ላይ የደረሰው ግፍና ሰቆቃ መንሳኤ ሆኖ ዛሬ ሚሊዮናት ኢትዮጵያውያን ፍራቻንና ለነገ መትረፍን ብልጠት አድርገን ከዚያም ባለፈ ለግፈኞች ማደግደግ የስልጡንነት መመዘኛ ሁሉ ሆኖ ተዋርደን እንኖራለን። የገዢዎቻችን አላማ የሕዝብን መንፈስ ማሽበርን በተመለከተ እየተሳካለት የሚገኝ ይመስላል። በአንድ ወቅት የገዢዎችን እሳቤ የሚሸነቁጥ ምርጥ ቲያትር የደረሰን ደራሲ ወያኔ 'በእንጀራው ሲመጣበት' በሳምንቱ የባህር ዳር ወጣቶችን 'በልማት' ተኮር ቲያትር ላይ ሲያስተምር አስተውለናል። እንዲህ እንዲህ አይነቱን እጅ መንሳት በየመንደሩ የምናስተውለውን ጭምር ከደማመርነው በርግጥም እነዚህ ሰዎች እየሆነላቸው ያለ ይመስላል ፍራቻና እጅ መስጠትን ማህበረሰብ ውስጥ ማስረጽን በተመለከተ። እባህር ማዶ የፓለቲካ ጥገኝነት ማመልከቻ አቅርቦ ተሳክቶለትም እወያኔ እግር ስር የሚወድቀውን ለቆጠረው ደግሞ አዎን በድህነታችንና በሰቆቃ ባደገ ስብዕናችን ላይ እነዚህ ሰዎች እየተጫወቱ መሆናቸውን አይስተውም። አንድ ወዳጄ በቅርቡ ሐገር ቤት ደርሶ የመጣን ጓደኛውን 'የህዳሴ ግድብ ' ምናምን እያለ ሲደሰኩር ከመቼው ደግሞ የወያኔ ደጋፊ ሆነህ አረፍከው አልኩት አለኝ። ቀድሞ ሲያውቀው ሰልፍ ካልወጣን ወያኔ ካልተቃወምን ነበር ነገሩ ሁሉ። ለመሆኑ ወያኔ ምንድን ነው ሲል ጠየቀኝ አለኝ። ወደ ፍራቻው ከትቶ ገባ ማለት ነው ኤሌ እድንጋያ እንደምትገባ። እናም ይህ ሰቆቃን መሰረት ያደረገ የአገዛዝ ፍልስፍናና ተግባር ኢትዮጵያን አልፎ ባህር ማዶ ድረስ ተሻግሮ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ቀፍድዶ ይዞ ይገኛል። በነገራችን ላይ የዚህ ጽሁፍ አላማ ይህ ሁሉ ግፍ እየደረሰበት ያለውን ማህበረሰብ ለመተቸት አይደለም የገዢዎቻችንን ስነ ልቦና የበለጠ ለመረዳት የአገዛዝ ዘዴያቸውን ለመቋቋም ምን መደረግ እንዳለበት በተለይም ፍራቻንንና ስቃይን ተቋቁሞ የሚያሸንፍ ብሄራዊ ስነ ልቦና እንዴት ማቆጥቆጥ እንደሚቻል ውይይት ለመክፈት እንጂ።

ሌላው የእነ መለስ የአገዛዝ መንገድ የድህነታችን አጋፋሪነታቸው ነው። በሐገር ቤት ካለው ኢትዬጲያዊ ጀምሮ በውጭ ሐገር እስከሚኖረው ሚሊዮናት ስደተኛ ድረስ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የዚሁ ሂደት ሰለባ ነው። እነ መለስ ከድሮም ጀምሮ እንወክለዋለን እንታገልልታለን የሚሉት የሕብረተሰብ ክፍል ' በድህነት ተቆራምዷል' ሀሳባችንን ይገዛል ከዚያም እሺ ብሎ ይገዛል የሚሉትን ነው። የኢትዮጵያ ገበሬዎችን ስቃይና ያጣ የነጣ ድህነት ያውቁ ስለነበር የእነርሱ ነጻ አውጪ ነን የገበሬ ጦርም ነን ሲሉ ጭምር ይሳለቁ ነበር። ጊዜ እንዳሳየን ነጻ እናወጣሃለን ያሉትን ገበሬ እየነዱ አራት ኪሎ ከገቡ በሁዋላ ተቃውሞ እንኳን ሲያሰማ እርሱና መሬቱ ያሉትን ትስስር ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ከመሬቱ ነው የሚነቅሉት። እከተማም ከገቡ በሁዋላ የበታችነት መንፈሳቸው ምንም አይነት የተማረና በብቃት የሰለጠነ ሰው ቢያገኙ በቀትር ብርሃን ይፈልጉ የነበረው ኑሮ ይደቁሳቸው የነበሩ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን ነው። ( እነ አባተ ኮሾን፤ አሊ አብዶን፤ እና ብዙ ቢጤዎቻቸውን ያስታውሷል)። አላማቸውም ስልታቸውም የግለሰቦችን ኢኮኖሚያዊ አቅመ ደካማነት ለፓለቲካ መሳሪያነት ማዋል ነበር። ለነገሩ ብዙዎች ገዥዎች ይህንኑ ዘዴ ነው የሚጠቀሙት።

እስደት ካሉት ኢትዮጵያውያን ጋር ያለውም ጨዋታ ከሞላ ጎደል የዚሁ ስልት አንድ አካል ነው ። በተጨናነቁ ቁጭራዎች ልጅነታቸውን ለገፉ ኢትዮጵያውያን ሐገር ቤት ጎጆ መቀለስ ማለት ብዙ ነገር ነው ። በድህነት ተወልዶ ላደገ ማህበረሰብ የንብረት ባለቤትነት ማለትም የማንነትና የስኬት መመዘኛ ዋንኛ ጉዳይም ነው። ይህንን የኢትዮጵያውያንን 'ረሀብ' መለስና ጓደኞቹ ጠንቀቀው ያውቃሉ። ተራ የማዘጋጃ ቤት ስራ የሆነውን መሬት መመራትና ጎጆ መቀለስ የኤምባሲዎቻችን ዋንኛ ተግባር የሆነው በዚህ ምክንያት ነው። በተገኘው አጋጣሚ ' ወያኔን' የሚረግም ወዳጅዎን የመንግስትን ጭቆና የሚቃወም ሰልፍ እንውጣ ሲሉ ግብዣ ያቅርቡለት ፤ " ሐገር ቤት የጀመርኳት ጎጆ ቢጤ አለች እርሷን ልጨርስ ባክህ " ይልዎታል። ከሀገር ቤት የሚመጣም የወያኔ መልዕክተኛ ድሀ አስተሳሰባችንን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ( መለስ እንዳስጠናው) የሰብአዊ መብት አልያም የፓለቲካ ውይይት አጀንዳ ያለው ስብሰባ አይጠራም ይኸው ሀያ አመት እንዳየነው ' የኢንቨስትመንት' ጥሪ ነው የሚያቀርብልዎ። እንግሊዞቹ የውሻ ሩጫ ቁማራቸውን ከውሾቹ በፊት በሚሮጥ ስጋ እንደሚያሳልጡት አይነት መሆኑ ነው። እናም የመንግስትን አይኑ ያወጡ ኢሰብ አዊና

ጭካኔ የተሞላባቸው ተግባራት መቃወምና አለመቃወም ቤት መስራት የመቻልና አለመቻል ጥያቄ ሆኖ እርፍ ይላል። እናም ያደግንበት ድህነትና እርሱንም ታቅፎ የሚያሞቀው 'የድሀ' ማህበረሰብ አመለካከትና ማህበራዊ ስነ ልቦና ካለማስተዋል የጥጋበኞችና ጎሰኞች መጫወቻ ሆኖ ያበቃል።

'መሪዎቻችን' የዛሬዎቹም ይሁኑ መጪዎቹ ከላይ ያነሳናቸውን ሁነቶች ጠንቅቀው የተካኑ ናቸው። አንድ የማውቀው ሰው የሚቀጥራቸውን የቤት ሰራተኞች ለምን እንደሚያንገላታ ስሞገተው መከላከያው " የቤት ሰራተኛ እናት አንድ ነች" ይለኝ ነበር። ሁሉም አስተሳሰባቸው አንድ አይነት ነው ለማለትና የእርሱን ጋጠወጥና ግፈኛ ባህሪ በእነርሱው 'ምግባረ ብልሹነት' ለማላከክ። እናም ለገዢዎቻችን ሁላችንም የተሰናከለ ሰብዕና ያለን መንጎች ነን። ፈረንጆቹ እንደሚሉት ብንመቻቸውም ባንመቻቸውም የተረገምን። (Damned do , damned if you don't.) እነርሱ እኛን እንደ ሰርከስ ፈረስ ባህሪያችንን እያረቁ 'የመምራት' ከባድ ሃላፊነት አለባቸው። ስዩመ እግዚያብሄርም ይሁኑ፤ ስዩመ አብዮታዊ ዲሞክራሲ። እንዴት አዋርደው እንደሚገምቱንና እስክንረዳና በቃኝ እስክንል ድረስ ።

ቸር እንሰንበት

« http://hassabnet.blogspot.com/»